

# መልካም ፋሲካ?
# መልካም የትንሳዔ በዓል?

ዛሬ በአውሮፓውያን አቆጣጠር፣ በሚቀጠለው ሳምንት ደግሞ በኢትዮጵያና በሌሎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ዘንድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሳዔ በዓል ይከበራል።

በክርስቲያን ኢትዮጵያውኖች ዘንድ አንድም 'እንኳን ለፋሲካ በዓል አደረስዎት' / 'እንኳን ጾመ ልጉዋሙን በሰላም ፈታልዎት' አንድም ደግሞ 'እንኳን ለብርሃነ ትንሳዔው በሰላም አደረሰዎት' በማለት ለክብረ በዓሉ ከምንጠቀምባቸው ዋነኛ የመልካም እና የደስታ ምኞት መግለጫዎች ናቸው።

በዚህች አጭር ጽሑፍ ልጠቅስ የምፈልገው ሦስት ሃሳቦች ናቸው።

1ኛ/ ፋሲካ - ጾም መፍታት ነው?
2ኛ/ የትንሳዔ ክብረ በዓል አጀማመር?
3ኛ/ ክርስቶስ መድኅኒታችን ተነስቷል!

'ዛሬ ፍስክ ነው'፣ 'በሰላም ፈሰካችሁ?' ከሚሉት አባባሎች እንደምንረዳው ፋሲካ ከጾም መፍታት ወይም በጾም ጊዜ የሚከለከሉትን የምግብ ዓይነቶች መመገብ የሚያመለክት ትርጉም አለው። ለነገሩ ፋሲካ ወይም የፋሲካ በዓል ከጾም ጋር በምንም አይገኛንም። *ፔሳክ* የሚለውን የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚተረጉም ቃል ነው። *ፔሳክ* እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ሊያወጣ ሲል እንዲያከብሩት ያዘዛቸው በዓል ነው። በእንግሊዘኛው Passover በማለት የሚታወቀው ይህ በዓል በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 12 ላይ በግልጽ ተጠቅሷል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከፈርኦን እጅ ባወጣበት ሌሊት፤ ለአራት ቀን ሲጠብቁት የነበረውን ጠቦት አርደው ደሙን በመቃናቸው እና በጉበናቸው ላይ እንዲቀቡና *ሥጋውን* ደግሞ ጠብሰው ከመራራ ቅጠልና ከቂጣ ጋር ፈጥነው እንዲበሉት ያዘዛቸው ሥርዓት ነው። የእግዚአብሔርን መታደግ እንዲያስታውሱ ይህንን በዓል በየዓመቱ በኒሳን ወር በ14ኛው ቀን አይሁዶች ያከብሩ ነበር። ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ በገበታ እራት ከነርሱ ጋር የበላው ይህንን በዓል በሚያከብሩበት ምሽት ነበር (The Lord's Supper በመባል የሚታወቀው)።

ታዲያ እንግዲህ ዛሬ ወይም በሚቀጥለው ሳምንት የምናከብረው በዓል ከመጾም ወይም ከመብላት ጋር የሚያያዝ በዓል አይደለም ማለት ነው? "የእግዚአብሔር ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና" (ሮሜ 14፥17)። ከሆነ ዘንዳ የትንሳዔ በዓል እንዴት መከበር ይገባዋል? እንዴት እንዲከበር ትዕዛዝ አለን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ትምህርቶችን፣ ብዙ ሥርዓቶችን፥ ብዙ የሕይወት መርኖችን በግልጽ እና በኃይል ሲደነግግ እና ሲያስታውቅ እንዲከበር የደነጋገቸው በዓላት የሉም። በኦሪት ዘመን እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን በርካታ ክብረ በዓሎችን ደንግጎላቸው ነበረ። በአዲስ ኪዳን ግን ከ'ጌታ እራት' / ከ'ቅዱስ ቁርባን' በስተቀር እንድናከብር ወይም እንድንጠብቅ ያዘዘን ሥርዓተ በዓል የለም። የታሪክ ማኅደር እንደሚዘግበው የክርስቶስ ልደት/የገና በዓል ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ፤ የትንሳዔ ወይም የፋሲካ በዓል ደግሞ ከሁለተኛውና ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ መከበር የጀመረ በዓል ነበረ። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የጌታዋን የክርስቶስን ሞትና ትንሳዔ ታስታውስ የነበረው በጥምቀት ሥርዓት - 'በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ' - ቆላስያስ 2፥12፤ እና በጌታ ራት ወይም በቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ነበር (1ቆሮንቶስ 11፥23-26)። ጾምና የትንሳዔ በዓል የተቆራኙበት ታሪክ እንደሚያስረዳው በዚያን ጊዜ የነበሩ አዲስ ክርስቲያኖች በዕብራይስጦቹ የፋሲካ በዓል ወቅት የሚውለውን የክርስቶስን ትንሳዔ በዓል ምክንያት በማድረግ ይጠመቁ ነበር። ለዚህም የጥምቀት ሥርዓት ዝግጅት ሲባል ሲጀመር የሁለት ቀን ወይም የ40 ሰዓት የጾም ሥርዓት ይደረግ ነበር።

ከዚያም የጾሙ ጊዜ ወደ ስድስት ቀናት፣ ወደ ሦስት ሳምንት በመጨረሻም ወደ 40 ቀን ደረሰ። በ325 ዓም ተሰብስቦ የነበረው የኒቂያ ጉባዔ ይህንን የጾም ጊዜ ለ40 ቀናት እንዲቆይ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁሉም የክርስትና ማዕከሎች (በሮም፣ በቆስጠንጢንያ እና በእስክንድሪያ) አንድ ዓይነት የጾም ሥርዓት እንዲኖር ደነገገ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተነስቶ የነበረው ችግር የትንሳዔው በዓል የሚውልበት ቀን ነበር። በመጀመሪያ የአይሁዶቹን ሥርዓት በመከተል የኒሳን ወር በገባ በ14ኛው ቀን ነበር የሚውለው። ከጊዜ በኋላ 1ኛ/ ከአይሁድ ሥርዓት ለመለየት ሲባል 2ኛ/ በዓሉ በማንኛውም ቀን ይውል ስለነበረ እሁድ ቀን እንዲውልና እንዲከበር ስለተፈለገ የአይሁዶች የፋሲካ በዓል በዋለ የመጀመሪያው እሁድ እንዲውል ተደረገ። ከዚያም በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አሊያም በሮም እና በምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት የአከባበር እና የቀን አቆጣጠር ልዩነት እየመጣ በምሥራቃውያን ማለትም በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በ40ዎቹ ቀናቶች ላይ ተጨማሪ ቀኖች መጨመር ተጀመረ። ለምሳሌ በምሥራቅ የሚገኙት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በ40 ቀናቶቹ ላይ የሕማማትን ሳምንት ሲጨምሩ ምዕራብያውያን ደግሞ ሕማማትን በ40ዎቹ ቀናቶች ውስጥ አካተቷቸው። እንግዲህ የአብይ ጾም አመጣጥ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል። በርግጥ ነው ጾም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ቢሆንም ለ40 ቀን ክርስቲያን እንዲጾም በግልጽ የሚደነግግ ደንብ ወይም ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ 40 የተለየ ቁጥር ሆኖ ስለሚታይ [በኖኅ ዘመን የዉሃ ሙላት ለ40 ቀናት ነበር፣ እሥራኤላዊያን በምድረበዳ 40 ዓመት ተንከራተቱ፣ ሙሴ በሲና ተራራ ሁለት ጊዜ ለ40 ቀናት ቆየ፣ ኤልያስ ከኤልዛቤል ሸሽቶ ለ40 ቀን ተደበቀ፣ የነነዌ ሰዎች ለ40 ቀናት የንሰሐ ጾም ጾሙ፣ በመጨረሻም ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ በበረሃ ለ40 ቀንና ሌሊት ጾመ] እንደዚሁም ከትንሳዔው ክብረ በዓል አስቀድሞ ለ40 ቀን እንዲጾም ተደነገገ።

ከጾሙም፣ ከቀናቱም ቁጥር ይበልጥ ለነፍሳችን እና ለመዳናችን ማዕከል የሆነው እውነት የክርስቶስ ከሞት መነሳት ነው። በመጀመሪያ ስለእኛ ኀጢአት ሲል የዕዳችንን ጽሕፈት ማለትም የእግዚአብሔርን ፍርድ እንድንቀበል የሚያደርገውን የክስ መሠረት - ማለትም ኀጢአት - ለመሻር ሕይወቱን በመስቀል ላይ አሳልፎ ሰጠ። ከዚያም የኛን የዘላለም ሕይወት ለማረጋገጥ ከሙታን በታላቅ ኀይል ተነሣ! ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክቱ እንደሚያስረግጠው፤ '**አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኗልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና**' – (ምዕራፍ 15፥20-23)።

ስለዚህ የትንሳዔ ክብረ በዓል መሠረቱና መካከለኛው ነጥቡ በእርሱ ትንሳዔ የአማኞች ትንሳዔ እርግጥ መሆኑን በመገንዘብ፤ በዚህ ሊገለጽ በማይችል ታላቅ ተስፋ ሐሴት በማድረግ ያለንበትን የመንፈሳዊ ሕይወት በመመርመር እግዚአብሔርን እያመሰገንን የምንውልበት ቀን፣ እርስበርሳችን 'ተነስቷል!' እየተባባልን የምንበረታታበት፤ ባማረ ዜማና ቅኔ የምንዘምርበት ዕለት ነው ማለት ነው። ዶሮ ወጡ፣ ድፎ ዳቦው፣ ጠላው፣ ወዘተ.... ቢኖር መልካም ነው። ብቻውን ለሥጋችን፣ ለሆዳችን የሚሆን የክብረ በዓል እንዳይሆን እግዚአብሔር አምላክ የማስተዋል እና የእውነት ጥበብ ይስጠን!

መልካም የትንሳዔ በዓል እየተመኘሁላችሁ የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በእርጋታ፣ በጥሞና እና በጸሎት መንፈስ ሆናችሁ እንድታነቡት እጋብዛችኋለሁ።

"ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ሕይወትን ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን"

ኤፌሶን 2፥4-7